# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 2 ቁጥር 61 ጥቅምት 26 ቀን 2013ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## < <እኛ ከሕወሓት ስንላቀቅ የትግራይ ሕዝብም ከሕወሓት ይላቀቃል፤ በነፃነትም መኖር ይጀምራል> >

### ብርሀኑ ነጋ （ፕሮፌሰር） የኢዜማ መሪ



# ቆይታ

## «በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚታወቁ፣ በሙያቸው ጥሩ እውቀትና ልምድ ያላቸው ሰዎች በፖሊሲ ሰነዶቻችን ላይ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ አድርገናል»

### ዳዊት በለው (ዶክተር)

የዛሬው የዜጎች መድረክ «የቆይታ» አምድ እንግዳ ዳዊት በለው (ዶክተር) ናቸው፡፡ ዳዊት በለው የኢዜማ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ኮሚቴ ሰብሳቢ ናቸው፡፡ በሰብሳቢነት የሚመሩት የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ኮሚቴ ምን ምን ስራዎችን ሲከውን እንደቆየ፣ በሥሩ ያሉት ዘርፎች ምን ስራእንደሰሩ፣ እንዲሁም በፖሊሲ ቀረፃ ሂደት ውስጥ ስላጋጠመው ተግዳሮቶች በሚመለከት ጥያቄዎች አንስተንላቸው አጠር ያለ ቆይታ አድርገናል፡፡ እንድታነቡት እንጋብዛለን፡፡ መልካም ንባብ!



*የፖሊሲና ጥናትና ምርምር ኮሚቴ በሥሩ ምን ያህል ዘርፎችን አቅፎ ይዟል እስካሁን ምን ምን ስራዎችን አከናውኗል?*

የኢዜማ የፖሊሲና ጥናትና ምርምር ዘርፍ የተለያዩ ክፍሎችን ይዟል፡፡ የፖሊሲ ዝግጅት፣ የስልጠናና አቅም ግንባታና የጥናትና ምርምር ክፍል ተጠቃሽ የሆኑ ክፍሎቹ ናቸው፡፡ የፖሊሲ ዝግጅት ዘርፍ የፖለቲካ መብቶችን ባረጋገጠ መልኩ ማለትም በፖለቲካ፣ በማኅበራዊና የኢኮኖሚያዊ ውሳኔ ትግበራ ሂደት ውስጥ እኩል እድሎችን በመፍጠር መልኩ ፍትሐዊ የሀብት ፈጠራና ተጠቃሚነትን ባረጋገጠ መልኩ እንዲሁም ፍትሀዊ የሆነ ማኅበራዊ አገልግሎት ክፍፍል እውን ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ፖሊሲዎችን ይቀርፃል፡፡ እነዚህ ፖሊሲዎችን ለመቅረፅ በፖሊሲና ጥናትና ምርምር ዘርፍ ውስጥ ቋሚ ኮሚቴ የማቋቋም ሥራ ተሰርቷል፡፡ በጥናትና ምርምር ቋሚ ኮሚቴ ዘርፍ ውስጥ 5 አባላት ያሉት ቋሚ ኮሚቴ በሥራ ላይ አለ፡፡ ይህ ቋሚ ኮሚቴ ለጥናትና ምርምር ዝግጅት የሚረዱ መመሪያዎችን ያዘጋጃል፡፡ ፖሊሲዎቹ ምን አይነት ቅርፅ መያዝ አለባቸው? ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተግባራትን የምናከናውንበት ፖሊሲምን አይነት መሆን አለበት? የሚል መመሪያም ያዘጋጃል፡፡ የፖሊሲ ዝግጅት ቡድኖችንም ይመሰርታል፡፡

*በኮሚቴው ውስጥ ያለው የስልጠናና አቅም ግንባታ ዘርፍስ ምን ምን ሥራዎችን ማከናወን ችሏል? አላማውስ ምንድነው?*

የስልጠናና አቅም ግንባታ ቡድን መሰረታዊ አላማው በእውቀትና በሥነምግባር የታነፀ የፓርቲ አባልን እውን ማድረግ ነው፡፡ የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብና ፖሊሲዎችን በሚመለከት ለአባላት ስልጠና በመስጠት ተመጣጣኝ የሚባል እውቀት ደረጃ ላይ እንዲገኙና ለማኅበረሰቡ አንድ ዓይነት ቋንቋ እንዲናገሩ ማድረግን እንደ ግብ ይዟል፡፡ ለስልጠና የሚያገለግል የስልጠና ማኑዋል ተዘጋጅቷል፡፡ የስልጠናው ማኑዋል ተሳታፊነትን የሚያበረታታና ተግባር ተኮር ይዘት ያለው ተደርጎ ነው የተዘጋጀው፡፡ በአዲስ አበባ በሚገኙ 23ቱም ወረዳዎች ያሉ የጥናትና ምርምር ኮሚቴ ኃላፊዎችን ስልጠናውን በመስጠት የስልጠናው ማኑዋል ምን ያህል አሳታፊና ተግባር ተኮር ነው የሚለውን ፈትሸናል፡፡ በቀጣይነትም ስልጠናው ለዞን አስተባባሪዎች የሚሰጥ ይሆናል፡፡
ከስልጠናው ማኑዋል ዝግጅት በተጨማሪም የማኅበረሰብ ውይይት የምንመራበት የፖሊሲ ማኅበረሰብ ውይይት መመሪያ ሰነድ ተዘጋጅቶ አልቋል፡፡ በየደረጃው ማን ስልጠናውን ይሰጣል? በምን ያህል ጊዜ ይሰጣል? በአንድ ጊዜ ስንት የፖሊሲ ትውውቅ ይካሄዳል? የማኅበረሰብ ስብስቡን እንዴት ማግኘት ይቻላል? የሚሉ ነጥቦች እየዳሰስን እንገኛለን፡፡ ይህንን ካጠናቀቅን በኋላ የመጀመሪያው እርምጃችን የሚሆነው ለዞን አስተባበሪዎች በማኅበረሰብ ውይይት ላይ ያተኮረ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ ቁልፍ ናቸው ብለን የለየናቸውን ፖሊሲዎቻችንን ከማኅበረሰቡ ጋር የማስተዋወቅ ሥራም የምንሰራ ይሆናል፡፡

*የጥናትና ምርምር ኮሚቴ የሥራ ድርሻስ ምንድነው?*

ከተለያዩ የፓርቲው ክፍሎች የጥናት ፍላጎቶች ይመጣሉ፡፡ የሚሰሩ ጥናቶች መጠይቆቹ ምን አይነት መሆን አለባቸው? ምን አይነት መጠይቅ መጠቀም ያስፈልጋል? የሚለውን የሚመልሰው ይህ ክፍል ነው፡፡ ለምርጫ ቅስቀሳ የሚሆን ምን አይነት የበጀት ማግኛ ዘዴዎች ብንጠቀም ጥሩ ነው? የሚለውን ለመለየት መጠይቅ አዘጋጅተን በየምርጫ ወረዳዎቹ በትነናል፡፡ ከየምርጫ ወረዳ የሚመጡ ሀሳቦች በየወረዳዎቹ ከተዋቀሩ በኋላ ተገቢ የሆነ ገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን እያንዳንዱ የምርጫ ወረዳ የሚጠቀምበትን ስትራቴጂ የምንነድፍ ይሆናል፡፡

በፖሊሲ ቀረፃ ሂደት ውስጥ የፓርቲ አባላት ነው ተሳታፊ የሆኑት ወይስ ባለሙያዎችን ነው አሳታፊ ያደረጋችሁት? በአብዛኛው የፖሊሲ ዝግጅት ቡድኖች ውስጥ ተሳታፊ የሆኑት የፓርቲ አባላት ያልሆኑ ምሁራንና በዘርፉ ልምድ ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡

*ምን ያሕል ቡድኖች አዋቅራችኋል? ምን ያህል ፖሊሲዎችን መቅረፅ ችላችኋል?*

ከ40 በላይ የሚሆኑ ቡድኖችን እንዲዋቀሩ ተደርገው ከ40 በላይ ፖሊሲዎች ተቀርፀዋል ፡፡

*የፖሊሲና ጥናትና ምርምር ኮሚቴ በእቅድ ደረጃ ምን ያህል የፖሊሲ ሰነዶችን ለመቅረፅ ነው አቅዶ የተነሳው?*

ፖሊሲ አንድ ጊዜ ሰርተኸው የሚያበቃ አይደለም፡፡ ሁልጊዜ የሚሻሻል ነገር ነው፡፡ ፖሊሲ የሚያስፈልጋቸው አዳዲስ የሥራ ዘርፎችም ሊመጡ ይችላሉ፡፡ እነዚህን ለማካተትና መፍትሔ ለመስጠት የፖሊሲ ዝግጅት ያስፈልገዋል፡፡ ያቀድነው ከ40 በላይ ሰነዶችን ለማዘጋጀት ነው፡፡ ቡድኖቹን ስናቋቁምም ይህንን ታሳቢ አድርገን ነው፡፡ እስካሁን ባለው ሂደት በማኅበራዊ ዘርፍ አገልግሎት 17፣ በኢኮኖሚ ዘርፍ 24፣ በፖለቲካው ዘርፍ 11 ፖሊሲዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህ ፖሊሲዎች ለኢዜማ ብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንዲመረምራቸውና እንዲያያቸው ለማቅረብ በሂደት ላይ ነን፡፡ እነዚህን ፖሊሲዎች ለብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በማቅረብ ይሁንታ እንዲያገኙ በመስራት ላይ ነው የምንገኘው፡፡

*የቀረፃችኋቸውን ፖሊሲዎች ከማቀናጀት (Integrate) አንፃር ምን ሥራ ሰርታችኋል?*

አስቀድሜ እንደገለፅኩልህ ፖሊሲዎቻችንን የቀረፁት ባለሙያዎች ናቸው፡፡ የምንፈልገው ደረጃ ላይ የደረሱትን ፖሊሲዎች እንደ ገና አውጥተን በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚታወቁ በሙያው ጥሩ እውቀትና ልምድ ያላቸው ሰዎች በፖሊሲ ሰነዱ ላይ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ አድርገናል፡፡ ለምሳሌ ያህል የባለሙያዎቹን አስተያየት ከተቀበልን በኋላ በማኅበራዊ ዘርፍ ላይ ብቻ ተቀናጅተው ሊሰሩ የሚገባቸው ፖሊሲዎች የትኞቹ ናቸው የሚለውን በመለየት ቅርፅ የማበጀት ሥራ ሰርተናል፡፡

ፖሊሲዎቹ እቅዳቸው ስኬታማ መሆኑን የሚለኩበት መለኪያ በጋራ ካላወጡ በተናጠል ሰርተው ውጤታማ አይሆኑም፡፡ ስለዚህም በጋራ መስራትአለባቸው ብለን የምናስባቸውን ፖሊሲዎች አንድ ላይ በማድረግ የቅንጅት ሥራዎች እየሰራን እንገኛለን፡፡

*በፖሊሲ ቀረፃ ሂደት ውስጥ ምን አይነት ተግዳሮቶች ገጥሟችኋል?*

የፖሊሲ ቀረፃ በቀላሉ የሚሰራ ሥራ አይደለም፡፡ የራሱ የሆኑ ችግሮች አሉት፡፡ ፖሊሲዎችን ለመቅረፅ የፖሊሲ ቡድን መመስረት አስፈላጊ ነው፡፡ የፖሊሲ ቡድን ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎችን ማግኘት በጣም ከባድ ነው፡፡ የነበረን የፖለቲካ ባህል አለ፡፡ ሰዎች ተቃዋሚ ወይም በዘመኑ ቋንቋ «ተፎካካሪ ፓርቲ» ውስጥ ገብተው ለመንግሥት ተፎካካሪ አካል ሆኖ መሳተፍን ይፈራሉ፡፡ የአብዛኛዎቹ ምሁራኖቻችን ችግር ይህ ነው፡፡

በፖሊሲ ቀረፃ ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ ፍቃደኛ ሆነው የመጡ ሰዎችም ኢዜማ፣ መንግሥትን ተችቶ ጠንከር ያለ መግለጫ በሚያወጣበት ጊዜ ደንግጠው ወደኋላ የመሸሽ ነገር አለ፡፡ ሌላው ያጋጠመን ችግር ወይም እንደ ተግዳሮት የሚነሳው ነጥብ ፖሊሲዎቻችንን የማስተቸት ስራ ስንሰራ በቂ የሆነ ባለሙያ አለማግኘት ነው፡፡ በተጨማሪም የፖሊሲ ቡድን አባላት በከፍተኛ ተነሳሽነት ስራ ይጀምሩና የፖሊሲ ስራ ጊዜ የሚወስድ፣ በእያንዳንዱ ረቂቅ ላይ ውይይት በማድረግ እርማት በመስጠት እንደ ገና መስራት የሚያስፈልገው ነው፡፡ ይህ አይነቱ ሂደት ወደኋላም ወደፊትም የሚወስድ አካሄድን የያዘ ነው፡፡ በዚህ ተሰላችተው ወደኋላ የሚያፈገፍጉ አሉ፡፡ በዚህ የተነሳም የፖሊሲ ቡድን መሪዎችን እስከመቀየር ደርሰናል፡፡

*የዘውግ ፖለቲካ በተንሰራፋበት ሀገር የፖሊሲ አማራጮችን በማቅረብ ለመወዳደር መሞከር ዘመኑን ያልዋጀ ፖለቲካ ማራመድ ነው በሚል ትችት የሚያቀርቡ ወገኖች አሉ፡፡ ይህን ትችት እንዴት ይመለከቱታል?*

የፖለቲካ ሂደት መቃኘት ያለበት በፖለቲካ አስተሳሰብ ነው፡፡ በማንነት ላይ መሆን አለበት የሚል እምነት የለኝም፡፡ ኢዜማ ውስጥ ያለው አስተሳሰብም ተመሳሳይ ነው፡፡ የዘር ፖለቲካ ላለፉት 27 ዓመታት ውስጥ የኖርንበት ነው፡፡ እዚህ ባህር ውስጥ ተነክረን ገና መውጣታችን ነው፡፡ አልደረቅንም፡፡ የዘውግ ፖለቲካ ለቅስቀሳ በጣም አመቺ ነው፡፡ ቁስል እየነኩ እንዲደማ ማድረግ ትችላለህ፡፡ ይህ አይነቱ ቅስቀሳ በምርጫ ወቅት ትልቅ ውጤት ሊያመጣ ይችላል፡፡ የዘውጌ ፖለቲካ ትኩሳቱ ገና ስላልበረደ የምርጫው ውጤት ላይ ተፅእኖ ሊያሳድር ይችል ይሆናል፡፡ አሸናፊ ይሆናል ወይስ ተሸናፊ? የሚለውን በሂደት የምናየው ነው የሚሆነው፡፡ አሁን ባለንበት ወቅት የአስተሳሰብ ፖለቲካና የዘውግ ፖለቲካን ስታወዳድራቸው የዘውጌ ፖለቲካ ጎልቶ የታየ ሊመስል ይችላል፡፡ አሁን ላይ ተፎካካሪ ሊሆን ይችላል፡፡ በሚቀጥሉት ምርጫዎች ግን የዘውግ ፖለቲካ ተቀባይነቱ እየቀነሰና ማኅበረሰቡ እየሰከነ ሁኔታዎችም እየተሻሻሉ ይሄዳል የሚል እምነት ነው ያለኝ፡፡

*ለቃለምልልሱ ፍቃደኛ ስለሆኑ በአንባቢዎቻችን ስም እናመሰግናለን!*

እኔም እንግዳ አድርጋችሁ ስለጋበዛችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ!


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ጥቅምት 26 ቀን 20113 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የትግራይ ሕዝብ ከሀገር መከላከያ ሠራዊት ጎን እንዲቆም ኢዜማ ጠየቀ።

ጥቅምት 19 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ(ኢዜማ) ሕወሓት በትግራይ ክልል በሚገኘው የኢፌዴሪ መከላለከያ ሠራዊት ላይ የከፈተውን ጥቃት አወገዘ፡፡

ፓርቲው ማክሰኞ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በማኅበራዊ ትስስር ገፁ ባወጣው መግለጫ ነው ጥቃቱን እንደሚያወግዝ ያስታወቀው፡፡ በመከላከያ ሰራዊቱ ላይ የተፈፀመው ጥቃትም በፍፁም ዝምታ ሊታለፍ እንደማይገባ እምነቱ መሆኑን ገልጿል፡፡ ‹‹በተለያየ ጊዜ ሕወሓት ሲያስተላልፋቸው የነበሩ የሥርዓት አልበኝነት ጥሪዎች እና በክልሉ ሕግን ተላልፎ ሲፈጽም የነበራቸው ድርጊቶች አልበቃ ብለው የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ምልክት የሆነው መከላከያ ሠራዊታችን ላይ የፈፀመው ጥቃት በፍፁም በዝምታ የሚታለፍ እንዳልሆነ እናምናለን›› ሲል ፓርቲው አቋሙን አስታውቋል፡፡ ‹‹የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት የሀገር አንድነት እና ሰላምን ለማስከበር የሚወስዳቸውን እርምጃዎች በመደገፍ የኢዜማ አባላት እና አመራር ከጎኑ እንደምንሰለፍ እናሳውቃለን›› በማለት የፓርቲው አባላትና አመራርም ከኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ጎን እንደሚሰለፉና ሠራዊቱ የሚወስዳቸውን እርምጃዎች እንደሚደግፉ ጠቁሟል፡፡

‹‹የትግራይ ሕዝብ የሚወሰደው እርምጃ ለሀገር አንድነት እና ሰላም ማስከበር ብቻ እንደሆነ በመረዳት ከሀገር መከላከያ ሠራዊት ጎን እንዲቆም እንጠይቃለን›› በማለት የትግራይ ሕዝብ ከሀገር መከላከያ ሠራዊት ጎን እንዲቆም ጥያቄ አቅርቧል፡፡

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብም ለሰላም እና ደህንነት እንቅፋት ከሚሆኑ ማንኛውም እንቅስቃሴዎች ተቆጥቦ አካባቢውን በንቃት እንዲጠብቅና ለሰላም እና ደህንነት መከበር ከፀጥታ አስከባሪዎች ጋር ትብብር እንዲያደርግ ኢዜማ ጥሪውን አስተላልፏል፡፡

## ፍርድ ቤቱ፣ በኢዜማና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር መሀል ያለውን ክርክር ለማድመጥ ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጠ

ጥቅምት 25ቀን 2013ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በአዲስ አበባ ከተማ በስፋት እየተፈጸመ ነው ያለውን የመሬት ወረራና ኢ-ፍትሐዊ የጋራ መኖሪያ ቤት እደላን በማስመልከት ጥናት እንዲደረግ ሰኔ 15 ቀን 2013 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ወስኖ ኮሚቴ በማዋቀር ወደ ሥራ መግባቱ ይታወቃል፡፡ የተቋቋመው ኮሚቴ ያደረገውን ጥናት ይፋ ካደረገ በኋላ በጉዳዩ ላይ ለመነጋገር እና መፍትሔ ለመፈለግ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር፣ ተበዳይ የሆኑ ነዋሪዎች፣ ምሑራን እና ባለድርሻ አካላትን ያካተተ ውይይት መስከረም 28 ቀን 2013 ዓ.ም ቢያዘጋጅም፣ የአዲስ አበባ መስተዳድር የከንቲባ ጽህፈት ቤት መስከረም 25 ቀን 2013 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ የተዘጋጀው ውይይት እንዲሰረዝ በማድረጉ ኢዜማ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት መውሰዱ የሚታወስ ነው፡፡

ፓርቲው ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት በመውሰድ ክስ በመመሥረት ለጥቅምት 25 ቀን 2013 ዓ.ም ቢቀጠርም ኢዜማ፣ ለተከሳሹ ለአዲስ አበባ መስተዳድር የፍርድ ቤት መጥሪያ ሲሰጥ መጥሪያውን የተቀበለው መስተዳድር ከፊርማ በተጨማሪ ማኅተም ባለማድረጉ ተመሳሳይ ፊርማ (ፎርጅድ) እየበዛ ስለሆነ ፍርድ ቤቱም ጥርጣሬ እንዳለው ጠቁሞ፣ በድጋሚ መጥሪያ ሲሰጥ በማኅተም ጭምር መቀበላቸውን እንዲያረጋግጡ እንዲደረግ በማሳወቅ በድጋሚ የ12 ቀናት የጊዜ ቀጠሮ መስጠቱን ጉዳዩን በቅርበት እየተከታተሉት የሚገኙት የሕግ ባለሙያው ኢዮብ መሳፍንት ለዜጎች መድረክ ገልጸዋል፡፡

የሕግ ባለሙያው እንደዚህ አይነት ነገር የተለመደ ባይሆንም አሳማኝ ምክንያት በፍርድ ቤቱ በመቅረቡ ድጋሚ መጥሪያ እንደሚያደርሱና በተቀጠረበት ቀን ፓርቲያቸው በአካል ቀርቦ ክርክር እንደሚያደርግ አስታውቀዋል፡፡





# ቀጣዩ ሀገር አቀፍ ምርጫ ለኢዜማ ያለው ፋይዳ የሚያሳይ ሥልጠና ተሰጠ

ጥቅምት 25ቀን 2013ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)ቀጣይ ሀገር አቀፍ ምርጫ ለኢዜማ ያለው ፋይዳ ምንድን ነው? የሚል መነሻ ሃሳብን መሰረት ያደረገ ሥልጠናመስጠቱን የኢዜማ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ ለዜጎች መድረክ ገለጹ፡፡

ኢዜማ፣ በአዲስ አበባ ከዚህ በፊት በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ የዞን አስተባባሪዎች እና ከምርጫው ጋር ተያይዞየምርጫ ወረዳዎችን የሚያስተባብሩ አስተባባሪዎችን በአንድ ላይ አድርጎ ሥልጠና መስጠቱን ያስታወሱትየድርጅት ጉዳይ ኃላፊው፣የተሰጠውን ሥልጠና ተከትሎ በፊት በሥልጠናው ላይ የተሳተፉትንበማካተት ከእያንዳንዱ የምርጫ ወረዳ ሊቀመንበር፣ ድርጅት ጉዳይ፣ ሕዝብ ግንኙነትና የፋይናንስ ኃላፊንያሳተፈ ሥልጠና ከጥቅምት 21 እስከ ጥቅምት 22 ቀን 2013 ዓ.ም መስጠቱን ገልጸዋል፡፡

የምርጫ ወረዳዎቹ አራቱ አመራሮች ከምርጫው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ስላላቸውሥልጠናው ወደሚሰጥባቸው ቦታ በማምጣት በ11 ማዕከላዊ ቦታዎች ላይ የመጀመሪያው ዙር ስልጠና መስጠቱንናበቀጣይ ሳምንትም በሌሎች 14 ቦታዎች ላይ ሥልጠና እንደሚሰጥ ኃላፊው ጠቁመዋል፡፡በአጠቃላይ ከ318 በላይ የሚሆኑ ምርጫ ወረዳዎችን ተደራሽ ለማድረግ እየተሰራ እንደሚገኝ ያስታወቁት ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው፣አሁን ባለው የሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ከጸጥታው ጋር ተያይዞ በቤንሻንጉል፣ በምዕራብ ወለጋ እና አፋር ሥልጠናውን መስጠት እንዳልተቻለክልሎቹ ወደቀድሞ ሰላማቸው ሲመለሱ ግን ሥልጠናውእንደሚሰጥ ገልጸዋል፡፡

ኢዜማ በወላይታ ዞን ሥልጠና እንደሚሰጥ ለሚመለከታቸውለመንግሥት ባለሥልጣናት በማሳወቅ ፍቃድ በማግኘት ለሥልጠናው አዳራሽ በመከራየት ሥልጠናውን ለማከናወን በዝግጅት ላይ እያሉ ‹‹ኮማንድ ፖስቱ መፍቀድአለበት›› በማለትመከልከላቸውንናከብዙ ውይይት በኃላ በሚቀጥለው ሳምንት ሥልጠናው እንዲሰጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መስማማታቸውን የድርጅት ጉዳይ ኃላፊውአስረድተዋል፡፡

በወረዳዎቹ ላይ የሚደረገው የምርጫ ዘመቻ ቀጣይ የምርጫ ሁኔታውን የሚወስን በመሆኑሥልጠና መሰጠቱን፣ ሠልጣኞችምወደ ምርጫ ወረዳዎቻቸው በመሄድ አመራሮችናአባሎችን እንደሚያሰለጥኑ፣ እስከ ታኅሣሥ ድረስ ሙሉ ዝግጅታቸውን አጠናቀው ወደ ሥራ እንዲገቡ እንደሚደረግ ዋሲሁን ተስፋዬ ገልጸዋል፡፡

# ‹‹እኛ ከሕወሓት ስንላቀቅ የትግራይ ሕዝብም ከሕወሓት ይላቀቃል፤ በነፃነትም መኖር ይጀምራል››

## ብርሀኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) የኢዜማ መሪ

ጥቅምት 26ቀን 2013ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)




የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ራሱን ለመከላከል ሕወሓት ላይ መውሰድ የጀመረው እርምጃ በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎችም ኃይልን ተጠቅመው የዜጎችን ደህንነት እንዲሁም የሀገር ሰላም እና አንድነት ላይ አደጋ በመጣል የፖለቲካ ዓላማቸውን ለማሳካት የሚንቀሳቀሱ ኃይሎችን በሙሉ ሥርዓት የሚያሲዝ እና ከአሁን በኋላ የፖለቲካ ዓላማን ለማሳካት ከሰላማዊ እና ሕጋዊ መንገድ ውጪ ለመንቀሳቀስ ያሉ አማራጮችን በሙሉ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ የሚዘጋ መሆን ይኖርበታል ሲል አሳሰበ ::

ፓርቲው ሐሙስ ጥቅምት 26 ቀን 2013 ዓ.ም በዋና ፅ/ቤቱ መስፍን ወልደማሪያም አዳራሽ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ነው ይህን ያለው፡፡ ‹‹የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት የሀገርን አንድነት እና ሰላምን ለማስከበር የሚወስዳቸው እርምጃዎች የኢዜማ አባላት እና አመራር ሙሉ በሙሉ ከጎኑ እንደሚቆም ለማረጋገጥ እንወዳለን›› በማለት የመከላከያ ሠራዊት እየወሰደ ያለውን እርምጃ እንደሚደግፍ አስታውቋል፡፡ መከላከያ ሠራዊቱ እና ሌሎች የመንግሥት የፀጥታ ተቋማት የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ የሚወስዷቸው እርምጃዎችም የሁሉንም ዜጎች ሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ያከበረ እንዲሁም ሰላማዊ ዜጎች በተለይም ሕፃናት፣ ሴቶች እና በዕድሜ የገፉ አረጋዊያን ማንኛውም ጉዳት እንዳይደርስባቸው አስፈላጊው ጥንቃቄ ሁሉ እንዲደረግ አሳስቧል፡፡

ኢዜማ ለትግራይ ሕዝብ በመግለጫው ባስተላለፈው ጥሪም አሁን እየተወሰደ ያለው እርምጃ የሀገር ሰላም እና አንድነትን የማረጋገጥ እርምጃ መሆኑ በማወቅ ለረጅም ጊዜ የስጋት ድባብ በመፍጠር እንደሸፋን እየተጠቀመ ሲበዘብዘው እና በስሙ ሲነግድ የነበረው ሕወሓትን በፍፁም ሳይተባበር ከሀገር መከላከያ ሠራዊት ጎን እንዲቆም የአደራ ጥሪውን ፓርቲው አቅርቧል፡፡

በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ ከጦርነቱ በኋላ የትግራይ ሕዝብ እጣ ፈንታ ምን ይሆናል? በሚል ከዜጎች መድረክ ለተነሳው ጥያቄ የኢዜማ መሪ ብርሀኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

የትግራይ ሕዝብ እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃ የሚወጣበት፣ በነፃነት መሪዎቹን መርጦ በሰላም ወጥቶ የሚገባበት ሁልጊዜ ምን አይነት ሰላይ ይመጣብኛል ብሎ ሳያዝንና ሳይፈራ የሚኖርበት ሁኔታ የሚኖርበት ትልቅ እድል መጥቶለታል ብዬ ነው የማምነው ያሉት መሪው፣ ሕወሓት የፈጠረው ግጭት ሲጠናቀቅ የትግራይ ሕዝብ ካለፉት 27 ዓመታት አንፃር ልክ እንደ ሌላው ኢትዮጵያዊ እኩል ሆኖ የሚኖርበት ሁኔታ ይፈጠራል ብለው እንደሚያምኑ ተናግረዋል፡፡ ‹‹ለትግራይ ሕዝብ የመጣበት ሳይሆን ለትግራይ ሕዝብ የመጣለት የነፃነት መንገድ ነው ብዬ ነው የማምነው›› በማለት መከላከያ ራሱን ለመከላከል በሕወሓት ላይ የወሰደው እርምጃ ለትግራይ ሕዝብ አሉታዊ ሳይሆን አዎንታዊ ነገር ይዞ እንደሚመጣ አስረድተዋል፡፡ ‹‹ሌሎቻችንን በመከራ ውስጥ ሲያኖረን የነበረው የሕወሓት አገዛዝ የትግራይንም ሕዝብ መከራ ውስጥ ሲያኖረው ነው የነበረው›› ያሉት መሪው ብርሀኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) ‹‹እኛም ከሕወሓት ስንላቀቅ የትግራይ ሕዝብም ከሕወሓት ይላቀቃል፤ በነፃነትም መኖር ይጀምራል›› ሲሉ ተደምጠዋል፡፡

‹‹የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግራይን ማኅበረሰብ እንደከዚህ በፊቱ አቅፎ የጋራ ሀገራችንን በጋራ የምንገነባበት ሁኔታ ይፈጥራል ብዬ ነው የማስበው እንጂ በትግራይ ሕዝብ ቂም ጥላቻ ኖሮት ያውቃል ብዬ አላምንም፤ ወደፊትም ይኖራዋል ብዬ አላስብም›› በማለት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከትግራይ ሕዝብ ጋር በፊትም ተከብሮና ተዋዶ ሲኖር እንደነበርና ወደፊትም በጋራ ኢትዮጵያን እንደሚገነባ ተናግረዋል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የፖለቲካ በሽታዎች በሙሉ ምንጫቸውም ‹‹እናውቅልሀለን›› የሚሉ የዘር ፖለቲከኞች እንጂ ሕዝብ እንዳልሆነ መሪው በአፅንኦት ተናግረዋል፡

ኢዜማ፣ ለትግራይ ክልል ፖሊስ እና ልዩ ኃይል አባላት ሕወሓት የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት ላይ ጥቃት እንዲደርስ በማድረግ በኢትዮጵያ አንድነት እና ሉዓላዊነት ላይ መዳከም እንዲፈጠር በሚያደርገው ሀገርን የማፍረስ ዘመቻ ላይ እንዳይሳተፉ ጥሪውን አስተላልፏል፡፡ ‹‹የትግራይ ክልል ፖሊስ እና ልዩ ኃይል በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ከኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ጎን በመቆምም ሕዝቡን ከስጋት እና ከአደጋ እንዲጠብቅ እንጠይቃለን፡፡›› በማለት ለትግራይ ክልል ፖሊስ እና ልዩ ኃይል ጥሪውን አቅርቧል፡፡



# አፅኖዖት

## የሚወሰደው እርምጃ ዘለቄታዊ ሰላም / መፍትሔ የሚያመጣ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል !

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) ከምስረታው ጀምሮ በማንኛውም መንገድ ሰላማዊ ካልሆኑ እንቅስቃሴዎች የታቀበ፣ የሚፈጠሩ ችግሮችን በውይይት ለመፍታት የሚጓዝ፣ አባላቱም በሰላማዊ መንገድ ትግል እንዲያደርጉ አጥብቆ የሚሰራ መሆኑን ከአመራርና ከአባላቱ በተጨማሪ በሌላውም የኅብረተሰብ ክፍል የሚታወቅ ነው፡፡ ይሄ አካሄዳችን አሁን ብቻ ሳይሆን ለወደፊትም የምንተገብረው መርሀችን ነው፡፡

ሕወሓቶች በተደጋጋሚ በሰላማዊ መንገድ ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ ቢጠየቁም በእምቢተኝነት ጸንተው ቆይተው በመጨረሻም የሀገር አለኝታ በሆነው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ላይ ጥቃት ፈጽመዋል፡፡ የሀገር መከላከያ ሠራዊት የአንድ ብሔር ተወካይ ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያ ሠራዊት በመሆኑ የተከፈተው ጥቃት በሀገር ላይ እንደተከፈተ ይቆጠራል፡፡ በሕወሓት በኩል የተከፈተው ጥቃት ተከትሎ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ራሱን ለመከላከል እና ለሀገር አንድነት እና ሰላም ከፍተኛ እና ተደጋጋሚ ስጋት ሲደቅን የነበረው የሕወሓት አገዛዝ ላይ መውሰድ የጀመረው እርምጃ በሌሎች የሀገራችን አካባቢዎችም ኃይልን ተጠቅመው የዜጎችን ደህንነት፣ ሰላምና አንድነትን አደጋ ላይ የሚጥሉ ኃይሎችን በሙሉ ሥርዓት የሚያሲዝ መሆን ይኖርበታል ብለን እናምናለን፡፡ እርምጃ መወሰድ አለበት ሲባልም እንደ ሀገር ወደፊት የሚኖረን ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም የሕግ የበላይነት ያለው ሚና ትልቅ ስለሆነና ይሄ እንዲከበርና ሕዝብም ሰላም እንዲያገኝ ከመፈለግ አንጻር መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ የሚወሰዱ እርምጃዎችም ዘለቄታዊ ሰላም የሚያመጡ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡

በክልሎች ልዩ ኃይል መካከል የሚደረገው ፍትጊያ ለማስቆም ይህን አይነቱን አደረጃጀት ወደ ክልል መደበኛ ፖሊስ፣ የፌደራል ፖሊስ ወይንም የኢፌዴሪ መከላከያ ወራዊት የሚቀላቀልበትን አሠራር መዘርጋት አስፈላጊ ነው ብለን እናምናለን፡፡ ይህን አቋማችንን ከዚህ ቀደምም መግለጻችን የሚታወስ ነው፡፡ በዜጎች መድረክ ሐምሌ 5 ቀን 2011 ዓ.ም በቅጽ 1 ቁጥር 001 ላይ ‹‹በፖለቲካ ምክንያት የመገዳደል አዙሪት ከመስተጋብሮቻችንና ከፖለቲካ መዝገበ ቃላችን ሊፋቁ ይገባል›› በሚል ዋና ርዕስ ሥር የክልሎች ልዩ ኃይል ሕጋዊ መሠረት የሌለው ከመሆኑም በላይ በክልሎች መካከል ያለው ልዩነት በወንድማማችነት መንፈስ ከመፍታት ይልቅ እንደተለያዩ ሀገራት እንዲተያዩ የሚገፋፋና የችግሮቹም መፍትሔ ከአፈ ሙዝ እንዲጠብቁ የሚያደርግ ሲሆን የማዕከላዊ የመንግሥትን ጥንካሬና ሕጋዊ ልዕልና የሚያኮስምን ተግባር ነው፡፡ በሂደትም ሀገራችንን ወደ ዘመነ መሳፍንት ስሪት የሚመልስ ዘረኝነት የተጠናወተው ኋላቀር አካሄድ ነው ማለታችን ይታወሳል፡፡

የችግሩም ማሳያ እንዲሆን ሐምሌ 2006 ዓ.ም በጋምቤላ ክልል የክልሉ ልዩ ኃይል ከመከላከያ ሠራዊት ጋር መዋጋቱ፣ ሰኔ 2008 ዓ.ም በአማራ ክልል በተፈጠረው ግጭት የክልሉ ልዩ ኃይል የግጭቱ አንድ አካል መሆኑ፣ በ2010 ዓ.ም በሱማሌና በኦሮሚያ ክልል ልዩ ኃይል መካከል በተፈጠረ ግጭት ለአንድ ሚሊዮን ዜጎች መፈናቀል ምክንያት መሆን፣ በቀድሞ የሱማሌ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አብዲ መሐመድ ኦማር (አብዲ ኢሌ) አደራጅነት የተቋቋመው ልዩ ኃይል ያደረሰው ጉዳት እንደ አብነት በመጥቀስ የክልል ልዩ ኃይሎች ከልክ በላይ በመታጠቃቸው ለፌዴራል መንግሥትም ከባድ የቤት ሥራ መሆናቸውንና ይህ አይነቱን አደረጃጀት መስመር ማስያዝ እንደሚገባ ማሳሰባችን ይታወቃል፡፡

አሁንም የትግራይ ልዩ ኃይል በመከላከያ ሠራዊት ላይ የፈጸመው ጥቃት ሀገሪቱን ለከፍተኛ ችግር ዳርጓታል፡፡ እነዚህን ችግሮች በማየት የፌዴራል መንግሥት በፊትም አሁንም የተፈጠረውን በመገንዘብ የትግራይ ልዩ ኃይልን ብቻ ሳይሆን በሁሉም ክልሎች የሚገኙ ልዩ ኃይሎችን ትጥቅ በማስፈታት የተደራጀውን ኃይል በማፍረስ ወደ ትክክለኛ መዋቅር እንዲገቡ እንዲያደርግ የሕዝቡንም ሰላም እንዲጠብቅ እንጠይቃለን፡፡

ዘንድሮ ሀገር አቀፍ ምርጫ ከመደረጉ አንጻር እነዚህ ልዩ ኃይሎች በፓርቲዎች እንቅስቃሴ ላይ ችግር ሊፈጥሩ የሚችሉ መሆናቸውን ታሳቢ በማድረግ የምርጫ ቅስቀሳ ከመጀመሩ በፊት መንግሥት በየክልሉ በስፋት የተደራጀውን ልዩ ኃይል ወደ ክልል መደበኛ ፖሊስ፣ የፌደራል ፖሊስ ወይንም የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት የሚቀላቀልበትን አሠራር መዘርጋት አለበት ብለን እናምናለን፡፡